# መጽሐፍ ቅዱስ ለህፃናት

## አቀራቢዎች



# ዳንኤልና
# የአንበሳው
# ጉድጓድ ፡፡

ጸሐፊው: Edward Hughes

ምሣሌ አቅራቢው: Jonathan Hay

ያሻሸለው (አሻሽሎ የጻፈው): Mary-Anne S.

የተተረጎመው: Zemendale Translation Service
email: zemendale@gmail.com
Po Box 32155, Addis Ababa, Ethiopia

አዘጋጁ: Bible for Children
www.M1914.org

©2024 Bible for Children, Inc.
ፈቃድ፡- ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ማባዛት ወይም ማተም ይቻላል
ነገር ግን ይህ መሆን የሚችለው ለሽያጭ ካላቀረባችሁ ብቻ ነው።

ዳርዮስ የባቢሎን አዲስ ንጉስ ነበረ፡፡ እጅግ ጠቢብ ነበረ፡፡ የእርሱን አገዛዝ እንዲረዱ ፣ አንድ መቶ ሃያ የሚሆኑ ሰዎችን ከመንግስቱ መካከል መረጠ፡፡ ከዚያም ለሶስቱ ኃላፊነትን ሰጣቸው፡፡ ዳንኤልም ከእነዚያ ሶስት ሰዎች መካከል ነበረ፡፡



ንጉስ ዳርዮስ ዳንኤልን እጅግ ያከብረው ነበረ ፤
በሁሉም ስፍራ ላይ ሊሾመውም ያስብ ነበረ፡፡



ሌሎቹ መሪዎች እጅግ ይቀኑ ነበረ፡፡ ከንጉሱጋ እንዲጣላ ለማድረግ
በዳንኤል ላይ የሆነች እንከን ለማግኘት ይፈልጉ ነበረ ::



ምንም ያክል ቢሞክሩም ፣ እነዚህ መሪዎች አንዳች ክፉ ነገር አላገኙበትም፡፡ ዳንኤልም በሚያደርገው ነገር ሁሉ በንጉሱ ፊት እውነተኛ ነበረ፡፡ ደግሞም ፣ በሚያደርገው ነገር ሁሉ ጠንቃቃና ጠንካራ ሰው ነበረ፡፡



ቀናተኛ የሆኑት መሪዎችም ዳንኤል ማታለል የሚቻልበት አንድ መንገድ ብቻ እንዳለ ያውቁ ነበረ። የእስራኤልን አምላክ ከማምለክ ሊከለክለው የሚችል አንዳች ነገር እንደሌለ ያውቁ ነበረ።





የዳንኤል ጠላቶች ዕቅድን ያወጡ ነበረ፡፡ ንጉሱ የሚፈርምበትን አንድ አዲስ ሕግ አደረጉ፡፡ ህጉም ፣ ሁሉም ሰው ወደ ንጉስ ዳርዮስ ብቻ ይጸልይ የሚል ነበረ፡፡ ይሔንን የሚ.ቃወም የቱኛውም ሰው ወደ አንበሳ ጉድጓድ ይጣል የሚል ነበረ፡፡

ንጉስ ዳርዮስ አዲሱን ሕግ ፈረመ፡፡



አዲሱ ሕግ ለዳንኤል ምንም አይነት
ለውጥን አላመጣም ነበረ፡፡ ሁልጊዜ
ያደርግ የነበረውን ነገር ማድረጉን
ቀጠለ፡፡ መስኮቱን ከፍቶ በቀን ሶስት
ጊዜ ይጸልይ ነበረ ፤ ወደ ሰማይ
አምላክም ይጸልይ ነበረ፡፡







ቀናተኛ የሆኑቱ
መሪዎችም በፍጥነት
ሔደው ለንጉሱ
ነገሩት፡፡ ዳንኤልን
ከማሰር ሌላ ንጉስ
ዳርዮስ ሌላ አማራጭ
አልነበረውም፡፡ ሕጉ
መከበር ነበረበት፡፡
ዳንኤልም መገደል
ነበረበት፡፡ ንጉሱ ብዙ
ሞከረ ፤ ነገር ግን ሕጉን
መቀየር የሚችልበት
ምንም አይነት መንገድ
አልነበረም፡፡

ዳንኤልም ወደ አንበሳው ጉድጓድ ለመጣል ሕግ ወጣበት። ወደ ተራቡት አናብስት ከመጣሉ በፊት ፣ ንጉስ ዳርዮስ እንዲህ አለው ፣ “ሁልጊዜ የምታመልከው አምላክህ ፣ ያድንሃል።”



ንጉሱ ያንን ምሽት አልተኛም ነበረ፡፡ በቀጣዩም ቀን
በማለዳ ፣ በፍጥነት ወደ አናብስቱ ጉድጓድ ሔደ፡፡





ንጉስ ዳርዮስም ጮኸ ፣
“ዳንኤል ፣ የሕያው አምላክ
አገልጋይ ፣ ሁልጊዜ
የምታመልከው አምላክህ
እግዚአብሔር ከአናብስቱ
አፍ አድኖሃልን?”
ምንአልባት ምላሽን አገኛለሁ
ብሎም አልጠበቀም ነበረ፡፡
ነገር ግን ዳንኤል መለሰለት፡፡

ዳንኤልም ተጣራ ፣
“ንጉስ ሆይ ፣
አምላኬ መልአኩን
ላከና የአናብስቱን
አፍ ዘጋ ፤ በዚያም
ምክንያት እኔን
አልጎዱኝም፡፡”
እንደገነም ፣ ንጉስ
ሆይ ፣ በአንተ ፊትም
ምንም ክፉ
አላደረግኩም፡፡”



ንጉስ ዳርዮስም ተደሰተ!
ዳንኤልም ከጉድጓድ ወስጥ
እንዲወጣ አዘዘው፡፡



ንጉሱም እግዚአብሔር ዳንኤልን እንዳዳነውና የዳንኤል ጠላቶች የእግዚአብሔር ጠላቶች እንደሆኑ አወቀ፡፡ እርሱን አሳስተውት ክፉን ሕግ ያስወጡት ሁሉ በአንበሳ ጉድጓድ ውስጥ እንዲጣሉ ትዕዛዝ አወጣ፡፡



ንጉስ ዳርዮስም የሰማይ አምላክ ታማኝ አገልጋዩን ዳንኤልን እንዳዳነው ዓለም ሁሉ እንዲያውቅ ፈለገ፡፡ ንጉሱም ሰው ሁሉ ሕያው አምላክን እንዲያመልክ ትዕዛዝ የሚሰጥ ሕግን አወጣ፡፡ ንጉሱም ዳንኤልን ወደክብርና ወደመሪነት መለሰው፡፡



ዳንኤልና የአንበሳው ጉድጓድ ፡፡

**ይህ ታሪክ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ**

ዳንኤል 6

**“የቃልህ ፍቺ ያበራል.”**
**መዝሙረ ዳዊት** 119:130

# መጨረሻ

ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ የሚያስተምረን ግሩም ስለሆነው አምላካችን እግዚአብሔር እኛን በመፍጠሩ እሱን እንድታውቀው ነው።

እግዚአብሔር “ኃጢአት” ብሎ የሚጠራውን ክፉ ነገር እንዳደረግን ያውቀዋል። የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው ነገር ግን እግዚአብሔር በጣም ስለወደደን አንዱንና ብቸኛው ልጁን ለቀራኒዮ መስቀል ሞት አሣልፎ በመሥጠት እንዲሞትና የኃጢአታችንን ዋጋ በእኛ ምትክ በመሞት እንዲከፍል አደረገው። ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ በኋላ በምድር ላይ ቆይቶ ወደ ሠማይ ወደ አባቱ አረገ! ያላመንን እኛም በኢየሱስ አዳኝት ብናምን እና ኃጢአታችንን ይቅር እንዲል ብለምነው ይቅር ይለናል። ደግሞም ያደርገዋል። እሱም በእኛ ውስጥ ይኖራል፤ እኛም በእርሱ ውስጥ ለዘላለም እንኖራለን አሜን።

ይህ እውነት እንደሆነ ካመናችሁ፣ እግዚአብሔርን እንዲህ በሉት
ጌታ ኢየሱስ ሆይ አንተ አምላክ እንደሆንክ አምናለሁ ነገር ግን ለእኔ ኃጢአት ለመሞት ስትል ሰው ሆንህ አሁን ደግሞ ህያው ነህ። እባክህ ወደ ህይወቴ ግባ ኃጢአቴን ይቅር በል በዚህም አዲስ ህይወት አሁን ይኖረኛል አንድ ቀን ከአንተ ጋር ለዘልዓለም ለመኖር ወደ አንተ እመጣለሁ። ለአንተ እንድኖርና እንደ ልጅ እንድታዘዝልህ እርዳኝ። አሜን።

በየዕለቱ መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ ከእግዚአብሄር ጋር ተነጋገር! የሐ. 3.16